እንድንሚላ እንተጋገዝ

አንድ ቀበጥ ልጅ የነበራት አንዲት እናት ነበረች፡፡ ገጽታዋ ሁሉ በእሳት የተለበለበ ነበር፡፡ ያያት ሁሉ ይገረማል፡፡ አንዳንዱም ደንግጦ ይሸሻል፡፡ በተለይ ልጇ በእናቱ ገጽታ ስለሚያፍር አብሯት መታየትም ሆነ ትምህርት ቤት አብራው እንድትሄድ አይፈልግም ነበር፡፡ ለአንዳንድ ጓደኞቹ እናቴ ሞታለች፣ ለሌሎቹም እናቴ ውጭ ሀገር ሄዳለች እያለ ነበር የሚነግራቸው፡፡

ከፍ አለ፡፡ ከኮሌጅም ወጣ፡፡ ትልቅ ባለ ሥልጣን ሆነ፡፡ በየሚዲያውም ስሙ ይጠራ ነበር፡፡ ሰዎችም ከእርሱ ጋር መገናኘትን እንደ ብርቅ ያዩት ነበር፡፡ መቼም ቢሆን ግን ጓደኞቹንም ሆነ ሌሎች ወዳጆቹን ወደ ቤቱ ለማምጣት አይደፍርም ነበር፡፡ በድንገት ወደ ቤቱ ለመጡትም ቢሆን ያቺን ምስኪን እናቱን የቤት ሠራተኛዬ ናት እያለ ነበር የሚያስተዋውቃቸው፡፡

አንድ ቀን እንዲህ ሆነ፡፡

እናቱ ጠራቺው፡፡ እያንጎራጎረ መጣ፡፡ ፊት ለፊቱ ተቀመጠች፡፡

«ለመሆኑ ለምን እነደዚህ እንደሆንክ ታውቃለህ?» አለቺው

«ስትፈጠሪ እንደዚህ የሆንሽ ይመስለኛል» አላት፡፡

«አይደለም፡፡»

አንድ ፎቶ ግራፍ አወጣችና አሳየቺው፡፡ እጅግ በውበት የተጥለቀለቀች ለግላጋ ወጣት ሴት፡፡

«ማናት?» አላት፡፡

«ከጀርባው ተመልከተው» አለቺው፡፡

ጀርባውን ገልብጦ አየው፡፡ የእናቱ ስም ተጽፏል፡፡ ከሠላሳ ዓመታት በፊት የተነሣ ፎቶ ነው፡፡

«አላምንም» አለ ደንግጦ፡፡

«ታምናለህ» አለቺውና ሌላም ሰጠቺው፡፡

ትምህርት ቤት ከጓደኞቿ ጋር የተነሣቺው ፎቶ ግራፍ ነበር፡፡ ሌላም ሠለሠችለት፡፡

ታድያ ለምን እንደዚህ ሆንሽ አላት አፍጥጦ፡፡

«ታሪኩ እንዲህ ነው» አለቺው፡፡

«አንድ ቀን አንተ የአሥር ወር ሕፃን እያለህ ዕንቅልፍ ወስዶህ አልጋ ላይ ተኝተህ ነበር። እኔ እህል ላሰጣ ውጭ ነበርኩ። እህሉን አስጥቼ ዘወር ስል ቤቱ በእሳት ተያይዟል። ለካስ ቡታ ጋዙ ኢጋድሎ ቤቱ በእሳት ተያይዟል። ኡኡ ብዬ ጮኽኩ። ሠፈሩም ተሰባሰበ። ሁሉም እሳቱን ለማጥፋት እንጂ አንተን ለማውጣት አላሰቡም ነበር።

«በእሳቱ መካከል እንደ ቅዱስ ገብርኤል ገባሁበት። አንተን በብርድ ልብሱ ሸፍኜ አምላኬን እየተማጸንኩ በፍጥነት ይገፍህ ወጣሁ። ያኔ የኔ ልብስ በእሳት ተያይዞ ነበር። ከፊሉ አካሌም በእሳቱ ተጎድቶ ነበር። አንተን ከሥለስቱ ደቂቅ የለየህ እነርሱ ጢስ ሳይነካቸው መውጣታቸው ነው። አንተን ግን ጢሱ ቢያፍንህም እሳቱ ግን አልነካህም። የአንተን እሳት እኔ ተቃጠልኩልህ።

«አየህ ልጄ። ያንተ ቃጠሎ እና ጉዳት እኔ ላይ ነው። የእኔ ጤና እና ውበት ደግሞ አንተ ላይ ነው።

«ያን ጊዜ ለራሴ አድልቼ ብተውህ እኔ በጤና መኖር እችል ነበር። አንተ ግን ዛሬ በሕይወት አትኖርም ነበር።»

ልጁ ራሱን ይዞ ጮኸ። እንደ ዕብድ እየጮኸም እናቱ እግር ሥር ተደፋ።

በሦስተኛው ቀን ጓደኞቹን ሰበሰበ። እናም እንዲህ አላቸው።

«እናቴ ይህቺ ናት። የርሷ ውበት እኔ ጋር ነው። ይእኔ መከራ እና ጉዳት ግን እርሷ ላይ ነው።» አላቸው ይባላል።

ለመሆኑ አካል ጉዳተኞች የማንን ጉዳት ነው የተጎዱት?

እንደ እኔ እምነት የሁላችንን ጉዳት ነው የተጎዱት። አንድ ማኅበረሰብ ሁሉም ጤነኛ፣ ሁሉም አካል ጉዳተኛ ሊሆን አይችልም። የኛ ጤንነት የኛ ብቻ አይደለም የእነርሱም ነው። የእነርሱ ጉዳትም የኛ ጭምር ነው። ስለ አካል ጉዳተኞች ስናስብ ስለ ተጎዱ ስለ ሌሎች ሰዎች አይደለም የምናስበው። ስለተጎዳነው ስለ እኛ ነው የምናስበው። የተጎዱት የማኅበረሰቡን ጉዳት ነው። የተሸከሙትም የማኅበረሰቡን ሸክም ነው። የሚቀበሉት ፈተና የማኅበረሰቡን ፈተና ነው።

ለአካል ጉዳተኞች የምናደርጋቸው ነገሮች የቸርነታችን፣ የደግነታችን፣ የቸሮታችን፣ የአዛኝነታችን ውጤቶች አይደሉም። እኛ ለእኛ የምናደርጋቸው የሰውነት ግዴታዎቻችን ናቸው። የእኛ መከራ እነርሱ ላይ የእነር ሱም ጤና እኛ ላይ ነው።

ማኅበረሰብ አንዱ ያለ አንዱ ሊኖር አይችልም። የማያስፈልጉ ዜጎች የሉም። እጅግ የሚያስፈልጉ ዜጎችም የሉም። አንዱ የሌላው ጥገኛ መሆኑ የሰውነት ግዴታ እንጂ የአካል ጉዳተኛነት ውጤት አይደለም።

የዳንኤል ዕይታዎች
Daniel kibret's Views
www.danielkibret.com

አካል ጉዳተኛነት ከሰዎች ጋር የሚኖር ነው። አንዳንዶች አጋጥሟቸው ተጋፍጠውታል። ሌሎቻችን ሰምተ ነው እና አይተነው ብቻ እናውቀዋለን። ዛሬ አካል ጉዳተኞች ብለን የምንጠራቸው ወገኖቻችን ግን የኛን ችግር ተጋፍጠው፣ የኛን ሕመም ታምመው፣ የኛንም ገፈት ቀምሰውልናል።

ለእነዚህ ወገኖች ክብር መስጠት፣ ክብካቤ ማድረግ እና መብቶቻቸውን መጠበቅ ለማንም የሚደረግ ተግባር አይደለም ለእኔ የሚደረግ ነው። ለራሴ።

ሰው በራሱ ሙሉ አይሆንም። አንዳችን የሌላችን ማሟያ ነን። አንዳችንም ያለ ሌላችን ሙሉ አንሆንም።

በሀገራችን እንዲህ የሚባል ነገር አለ። አንድ ማየት የተሳነው እና መራመድ የተሳነው ጓደኛሞች ነበሩ። በዚያው መንደር ደግሞ የአንድ የወይን እርሻ ባለቤት ነበር። ሰው ሁሉ ከዚያ የወይን ማሳ ገብቶ የፈለገውን ይወስድ ዘንድ ተፈቅዶለት ነበር። ሁለቱ ግን ተከለከሉ።

ምክንያት? ሲባል

ይህም አያይም ያም እንደ ሌላው ሆኖ አይራመድም ተብሎ። እነዚህ ሁለቱም ለየራ ሳቸው ጉዳታቸውን እንጂ ጥንካሬያቸውን አስበውት አያውቁም ነበር። አንድ ቀን ግን ተማከሩ። አንተ በእኔ እግር ሂድ፣ እኔም በአንተ ዓይን ልይ ተባባሉ። እናም ወደ ወይኑ ሥፍራ ሄዱ። ባለቤቱም ምንም አያመጡም ብሎ ትታቸው ሄደ።

ማየት የተሳነው እግሩ የተንዳውን ጓደኛውን ትከሻው ላይ ሸኮኮ አለው። ያም በጓደኛው ትከሻ ላይ ሆኖ ባለቤቱ መምጣት አለመምጣቱን መጠበቅ ጀመረ። ማየት የተሳነውም በእጆቹ እስኪበቃው ወይኑን ሸመጠጠ። በኋላም ባለቤቱ ሲመጣ ማየት በተሳነው እግር እየሮጡ፣ እግሩ በተንዳው ዓይን እያዩ አመለጡ።

ይህንን ያየ ባለቤቱም

ሐንካስ በእግረ ዕውር ሖረ፣

ዕውርኒ በዓይነ ሐንካስ ነጸረ፣

ወበክልኤሆሙ ወይንየ ተመዝበረ፣ አለ ይባላል።

ከተባበርን የማንወጣው ችግር የለም።

በዓለም ዐቀፍ የአካል ጉዳተኞች ቀን

በኢትዮጵያ የስብሰባ ማዕከል የቀረበ

ኅዳር 23 ቀን 2004 ዓም